**ለኮሌራ ወረርሽኝና ሌሎች የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች እንዲሁም ለተፈናቃይና ተመላሽ ወገኖች እየተሰጠ ያለውን የጤና ምላሽ <u>አስመልክቶ የተዘጋጀ ሳምንታዊ መግለጫ</u>**

**የኮሌራ ወረርሽኝን በተመለከተ**

- በአማራ እና በሱማሌ ክልሎች ተከስቶ የነበረው የኮሌራ በሽታ ወረርሽኝ ከቆመ ከአንድ ወር በላይ ስለሆነው በአለም አቀፉ የጤና ድርጅት መመሪያ መሰረት ክልሎቹ በአሁን ወቅት ከወረርሽኙ ነፃ መሆናቸውን እናረጋግጣለን ይሁንና ወረርሽኙ በተበከለ ምግብና ውሃ አማካኝነት በቀላሉ የሚተላለፍ በመሆኑ ህብረተሰቡ ሳይዘናጋ አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርግ እናሳስባለን፡፡

○ በዚህ ሳምንት በሀገር አቀፍ ደረጃ 44 ሰዎች በበሽታው ተይዘው የነበረ ሲሆን ከባለፈው ሳምንት ጋር ሲነፃፀር በበሽታው የተያዙ ሰዎች ቁጥር ቀንሷል፡፡ በአሁኑ ወቅት 16 ሰዎች (በኦሮሚያ 12፣ ትግራይ 2 እና በአዲስ አበባ 2) በለይቶ ማከሚያ ማዕከላት ውስጥ እየታከሙ ሲሆን ቀሪዎቹ የህክምና ድጋፍ ተደርጎላቸው ወደ መደበኛ ህይወታቸው ተመልሰዋል፡፡

○ እስካሁን በተደረገው የላቦራቶሪ ምርመራ በአጠቃላይ በ32 ናሙናዎች ላይ ቪብሮ ኮሌሬ ተገኝቷል፡፡

○ በሽታው ከተቀሰቀሰ ጀምሮ ከወረርሽኙ ጋር በተያያዘ በሀገር አቀፍ ደረጃ 18 ሰዎች ህይወት አልፏል ከነዚህም ውስጥ 14 በአማራ ክልል (6 በጤና ተቋም 8 ደግሞ በማህበረሰብ ውስጥ እያሉ ህይወታቸው ሊያልፍ ችሏል)፣ 3 በኦሮሚያ ክልል እንዲሁም 1 በአፋር ክልል ናቸው፡፡

  ○ በኦሮሚያ ክልል እስከ አሁን ድረስ 381 ሰዎች በወረርሽኙ ተይዘው የነበረ ሲሆን በምዕራብ ሀረርጌ ዞን በጭሮ ወረዳ 103፣ በኦዳ ቡልቱም ወረዳ 132፣ በሜኤሶ ወረዳ 41 ፣ በገመቺስ ወረዳ 13፣ ጉሜ ቦርደዴ 24 እንዲሁም በበዴሳ ከተማ 48 እንዲሁም በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን በሰንዳፋ ከተማ 18 ሰው እንዲሁም በበራክ ወረዳ 2 ሰዎች ተይዘዋል፡፡

○ እስካሁን ድረስ በአዲስ አበባ በበሽታው የተያዙ ሰዎች ቁጥር 137 ነው፡፡

  ▪ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ 26 ሰው፣ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ 36 ሰው ፣በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ 16 ሰው፣ በልደታ ክፍለ ከተማ 10 ሰው፤ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ 2 ሰው፣ በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ 11 ሰው፣ በጉለሌ ክፍለ ከተማ 4 ሰው፣ በቦሌ ክፍለ ከተማ 5፣ በየካ ክፍለ ከተማ 7 ሰው፤ በአራዳ ክፍለ ከተማ 14 ሰዎች እንዲሁም ቋሚ የመኖሪያ አድራሻ የሌላቸው 6 ሰዎች በበሽታው ተይዘዋል፡፡

○ እስካሁን ድረስ በትግራይ ክልል በበሽታው የተያዙ ሰዎች ቁጥር 22 ሲሆን ምስራቃዊ ዞን፣ መቀሌ ከተማ አስተዳደር፣ ደቡባዊ ምስራቅ ዞን እና ሰሜን ምዕራብ ዞን በበሽታው የተጠቁ ዞኖች ናቸው፡፡

○ በአጠቃላይ በሀገራችን በኮሌራ ወረርሽኝ የተያዙ ሰዎች ቁጥር 930 ደርሷል (በኦሮሚያ ክልል 375፣ በአዲስ አበባ 137፣ በትግራይ ክልል 22፣ በአፋር ክልል 154፣ በአማራ ክልል 202፣ በድሬዳዋ 1ና በሶማሌ ክልል 33) ፡፡

**ወረርሽኙን ለመቆጣጠር እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት**

- በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሃረርጌ ዞን የኮሌራ ክትባት በባለፈው ሳምንት የተጀመረ ሲሆን እስከ አሁን 256,564 ወይም 90 ፐርሰንቱን የተከተበ ሲሆን የክትባት ዘመቻው በቀጣይ ቀናት የሚጠናቀቅ ይሆናል፡፡
- በአፋር ክልል አሚባራ ወረዳ የኮሌራ ክትባት በትላንትናው እለት መሰጠት ተጀምሯል፡፡ በመርሃግብሩ መሰረት ከ60,000 በላይ ለሚሆኑ የኢንቨስትመንት እርሻ ላይ ለሚሰሩ የቀን ሰራተኞችና ለአከባቢው ማህበረሰብ የሚሰጥ ይሆናል፡፡
- በአሚባራ ወረዳ በባደሃሞ ቀበሌ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እጥረት ለመቅረፍ በተበላሸ የቧንቧ ውሃ መስመር ላይ በወረዳው ውሃ ቢሮ አማካኝነት ጥገና ተከናውኗል፡፡
- በአዲስ አበባ ከተማ የወረርሽኙን ስርጭት ለመግታት እንዲቻል የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ መንገዶችን በመጠቀም መልእክት እየተላለፈ ይገኛል፡፡
- በቀጣይ ቀናት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ታዋህዶ ቤተክርስቲያን የሚከበረውን የቅዱስ ገብርኤል አመታዊ ክብረ በአል ብዙ ህዝብ የሚሰባሰብበት በመሆኑ በዓሉ በሚከናወንበት አከባቢዎች ወረርሽኙ እንዳይከሰት ምእመናንና ቤተክርስቲያን ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለማስቻል በሚቀጥለው ሃሙስ የምክክር መርሃ ግብር በኢትዮጵያ የህብረተስብ ጤና ኢንስቲትዩት የተዘጋጀ ሲሆን በፕሮግራሙም ከ400 በላይ የሚሆኑ የአድባራትና የገዳማት አስተዳዳሪዎች እንዲሁም የስብከተ ወንጌል ሃላፊዎች የሚሳተፉበት ይሆናል፡፡

- የወረርሽኙን ስርጭት ለመግታት ወረርሽኙ በተከሰተባቸውና ባልተከሰተባቸው አከባቢዎች ህብረተሰቡ የአካባቢና የግል ንፅህና አጠባበቅ ስራዎችን በማከናወን እንዲሁም ለበሽታው መስፋፋት አጋላጭ የሆኑ ሁኔታዎችን በመለየት ወረርሽኙን ለማጥፋት እንዲረባረብ ኢንስቲትዩቱ ያሳስባል፡፡
- ከወረርሽኙ ጋር በተያያዘ የኢንቨስትመንት ኮሪደሮች ሰራተኞቻቸው በካምፕ ውስጥ የሚኖሩ በመሆናቸው ከአኗኗር ዘይቤአቸው ጋር በተያያዘ ለወረርሽኞች ያላቸው ተጋላጭነት ከፍተኛ በመሆኑ ለበሽታው ትኩረት በመስጠት ለሰራተኞቻቸው የንፁህ ውሃ አቅርቦትና የመፀዳጃ ቦታ እንዲያመቻቹ ኢንስቲትዩቱ ይጠይቃል፡፡

**ችኩንጉኒያ**

- በሶማሌ ክልል በቀብሪ ዳሃር ከተማ ተከስቶ የነበረው የችኩንጉኒያ ወረርሽኝ ሙሉ በሙሉ ቆሟል፡፡

**የተፈናቀሉና ወደ ቀዬቸው የተመለሱ ወገኖችን በተመለከተ የተከናወኑ ተግባራት**

- ለተፈናቀሉና ለተመላሽ ወገኖች በሚገኙባቸው ወረዳዎች የግልና የአከባቢ ንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችና ግበአቶች ( 203,000 ሳሙናዎች፣ 9000 የሴቶች የንፅህና መጠበቂያ ፓድና ከ 16ሺህ በላይ ጀሪካኖች) እንዲሁም 1.3ሚሊዩን በላይ የውሃ ማከሚያ ኬሚካሎች ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- ተፈናቃይና ተመላሽ ወገኖች በሚገኙባቸው ወረዳዎች ወረርሽኞች እንዳይከሰቱ የቅድመ መከላከል ተግባራት ማለትም የበሽታዎች ቅኝትና አሰሳ ተጠናክረው እየተከናወኑ ይገኛሉ፡
- ከግንቦት 24- ሰኔ15፣ 2011 ዓ.ም ድረስ ከ9ሺህ በላይ በሽተኞች የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ከ2000 በላይ እናቶችና ህፃናት እንዲሁም ሴቶች የስነተዋልዶ ጤና አገልግሎት አግኝተዋል፡፡
- በሶማሌ ክልል የስነ-አእምሮና የስነልቦና ድጋፍ አገልግሎት ከክልሉ በሰለጠኑ ባለሙያዎች አማካይነት በኮሎጂ የተፈናቃዮች ካምፕ እየተሰጠ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ ለተፈናቀሉና ለተመላሽ ወገኖች እንዲሁም ለተከሰቱ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች ምላሽ ለመስጠት ለመድሃኒትና የህክምና ቁሳቁሶች አቅርቦት፣ ለተመደቡ የሰው ሃይልና ለተሽከርካሪዎች ወጪ እንዲሁም ለክልሎች የስራ ማስኬጃ ድጋፍ ከሚያዝያ 23፣ 2011 ዓ.ም እስከ አሁን ድረስ ከ120 ሚሊዩን ብር በላይ ወጪ ሆኗል፡፡

**የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት**

**ሐምሌ 2 / 2011 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**